# ኃላፊነት ለሚሰማትና ለተባበረች

# ዓለም እውን መሆን

# የተዘጋጀ መድረክ

አዲስ አበባ

በሐምሌ 1986

በግራፔካ (GRAPECA) ተተረጎመ

# ኃላፊነት ለሚሰማትና ለተባበረች

# ዓለም እውን መሆን

# የተዘጋጀ መድረክ

አዲስ አበባ

በሐምሌ 1986

በግራፔካ (GRAPECA) ተተረጎመ

# የመድረኩ ታሪካዊ አመሰራረትና ዓላማዎች

## ታሪካዊ አመጣጡ

በ1986* እንደ ኤሮፓዊያን አቆጣጠር ፈረንሣይኛ ተናጋሪ የሆኑ እውቅ ሰዎችን ከተለያዩ ሀገሮች በማውጣጣት ያካተተ ቡድን "ፋውንዴሽን ፑር ላ ፕሮግረስ ደ ለሆም" ተብሎ በተሰየመና በስዊዝ ሀገር በተመዘገበ ነጻ ድርጅት አማካኝነት ተቋቋመ:: ቡድኑ የነዚህን እውቅ ሰዎች ጥያቄዎችና አመለካከቶችን በማቀናጀት ሁሉን አቀፍ በሆነ ድምጽ ለማንጸባረቅ ነበር የተመሠረተው:: ይህም ቡድን የተለያዩ ሃሳቦችን አቀናብሮ "የቪዜላይ ግሩፕ" በሚል በፈረንሣይ በቡርጋንዲ ከተማ ውስጥ ባለች የዩኒስኮ የዓለም ቅርሳ ቅርስ ፕሮግራም የሚካሄድባትን ከተማ ስም በመውሰድ የዚህን መድረክ ቀዳሚ ጥንስስ መሠረተ::

ይህ የቪዜላይ ግሩፕ ከፈረንሣዊው የህግ ባለሙያ ከሚስተር ካስሚየር ሞት በኋላ በተቀሩት ስምንት አባላት የተዋቀረ ነበር:: እነሱም የሚከተሉት ናቸው::

*በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የቀረቡት ቀናት በሙሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ነው::

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ካሊዮፕ ቢዮድ:- | የቪዜላይን የአንድ ቀን ዓውደ ጥናት አስተባባሪ - ፈረንሣዊ |
| 2. | ሚሸል ቢዮድ:- | ኢኮኖሚስት - ፈረንሣዊ |
| 3. | መሐመድ ሊርቢ ቡግራ:- | በቱኒዝ የሳይንስ ፋኩልቲ ፕሮፌሰር የሆኑ - ቱኒዚያዊ |
| 4. | ፒየር ካላም:- | የ"ፋውንዴሽን ፑር ለፕሮግሬስ ዳላሆም" ፕሬዚዳንት - ፈረንሣዊ |
| 5. | ቬናንት ኩቼ:- | የኢንተርናሽናል ፍልስፍናዊ ማህበረሰቦች ፌዴሬሽን የክብር ፕሬዚዳንት - ካናዳዊ |
| 6. | ሞሪስ ኮስንዴ:- | የፌደራል ፖሊ ቴክኒክስ ቦርድ የቀድሞ ፕሬዚዳንት የነበሩና የፋውንዴሽን ፑር ላፕሮግረስ ዳላሆም አባል - ከስዊትዘርላንድ |

7. ጆሴፍ ኪዘርቦ:- የታሪክ ተመራማሪ - ከቡርኪና ፋሶ

8. ሬኒ ሉበርት በተለያዩ መንግሥታዊ ተቋሞች ፕሬዚዳንት የሆኑ -ፈረንሣዊ

ከጥንስሱ ጀምሮ ይህ ቡድን ሰዎች በተፈጥሮአዊ አካባቢና በከባቢ አየር ላይ በሚያደርጉዋቸው እንቅስቃሴዎችና ድርጊቶች እንዲሁም በመስፋፋት ላይ ባሉ የባዮ-ቴክኖሎጂና ጦር-ነክ ያልሆኑ የኑክሌየር ኢንዱስትሪ ተግባራት የተነሣ በምድራችን ላይ የሚፈጥሩትን አደጋዎች ለማጥፋት ምርምር ማካሄድን ዋነኛ ዓላማው ለማድረግ የወሰነ ነበር::

በኦክቶበር 1987 የወጣው የቪዜላይ ቡድን መግለጫም የዚህን ችግር ሁኔታ ኢኮኖሚያዊ: ቴክኒካዊ: ፍልስፍናዊ ወይም አስተሳሰባዊና ፖለቲካዊ ሥር-መሠረቶችን የሚተነትን ነው::

በማርች 1988 ይኸው ቡድን "አቤቱታ ለዓለማችን ጠቅላይ መንግሥታት" በሚል ርዕስ ከተለያዩ እውቅ ግለሰቦች ጋር በመሆን አቤቱታውን አቀረበ:: የአቤቱታው ይዘት ያካተተው የፈረንሣይ ያሁለት ክፍለ-ዘመናት ብዙኃናዊና ግጥምጥም የለውጥ ክስተቶችን በመጥቀስ ለአዲሱ ማህበረሰብ መሠረት ጣለ::

አቤቱታውንም ወደ ዘጠኝ ቋንቋዎች ተርጉሞ በማሰራጨት ስፊ የድጋፍ ተሣትፎ ፊርማዎችን አጎረፈ።

ቡድኑ ካነሣቸው ጥያቄዎች ውስጥ የነበሩት የሰው ልጅ አዳዲስ ችግሮችን ለመጋፈጥ የሚያስችሉት አዳዲስ እምነቶችና እሳቤዎች አስፈላጊነት በዚህም እንጻር መንፈሳዊ ሳይንሳዊ፡ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኃይሎችንና ጥረቶችን ከሁሉም ሀገራት በመነጨ ጥረት የሚያስተጋብር ውጥን መኖር ዋነኞቹ ነበሩ። ቡድኑ የዚህን ቅንጅታዊ ሂደት "የዓለም ጠቅላይ-መንግሥታት ዝግጅት" (ፕሪፓሬሽን ኦፍ ፕላኔተሪ ስቴትስ-ጄኔራል) ብሎ ሰይሞታል።

ለዚህም ስኬት ከ1988 እስከ 1989 እና 1991 ባሉት የሥራ ጊዜያት ውስጥ ከተለያዩ ግለሰቦችና ቡድኖች ጋር በመተባበር ሁኔታውን በበለጠ ተንትኖ ለማብራራትና የድርጊት እቅዶችን (ፕሮፓዛል) ለመቅረጽ ተንቀሳቅሷል። እነዚህም የተለያዩ ስብሰባዎች "የአንድ ቀን የቪዜላይ ሴሚናሮች ተብለው የተሰየሙት ናቸው። በእነዚህ ውይይቶች ቡድኑ ለመረዳት እንደቻለው በሰው ልጅ አካባቢ ላይ የሚደርሱትን ጥቃቶችን ሥር ከሰደደው የምድራችን (የፕላኔታችን) ዝግመታዊ ሂደቶች ተጽዕኖና በተለይም "ሰሜንና

ደቡብ" ተብለው በተከፋፈሉት በበለፀጉና ኃላቀር በሆኑ ሀገሮች መሀል ካለው ግንኙነትና የችግር አጣብቂኝ ነጥሎ ማየት የማይቻል ሆኗል::

በዚህ መሀል የብራንድትላንድ ሪፖርት "የጋራ የወደፊት ትልማችን" በሚል ርዕስ የወጣው ዕትም የተለያዩ አፊሴላዊ የመገናኛ ብዙሃንና የተለያዩ ድርጅቶችን የትኩረት አቅጣጫ ወደ አካባቢና የተፈጥሮ ጉዳዮች እንዲሳብ አደረገ::

በሪዩ ዲጄኔር በሰኔ **1992** ውስጥ በተባበሩት መንግስታት ሥር የተካሄደው የመሪዎች መንግሥታት ስብሰባ **(Earth Summit)** ስለሁኔታው ሰፊ ግንዛቤን በማስጨበጥ አያሌ ውይይቶችንና ትንተናዎችን ለማስተናገድ አስችሏል:: በዚህም መሠረት ሀያ-አንደኛውን የስብሰባውን አጀንዳ ለማርቀቅ መንግሥታት ብቻ ሳይሆኑ የአካባቢና የዕድገት አቅጣጫን የማጣጣም ትኩረት ያላቸው ድርጅቶችና ተቋማት በአያሌ በይነ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች ላይ በተደረጉ ውይይቶች ተሣትፈውበታል:: አያሌ ግለሰቦችም የጋራ ጥናቶች ባካሄዱት "በአሥራ ሁለተኛው" የሥራ መርሃ ግብር እንዲሁም "ፋውንዴሽን ፎር ለፕሮግረስ ዲላሆም" ለእትም ባበቃው መሠረት ከድንጋጌዎቹ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው:: በተጨማሪም በቪዜላይ ቡድን

አባል በሆኑት መሐመድ ሰርቢ ቡጋራ አማካኝነት አንድ የልምድ ልውውጥ ሥርዓት ተቋቁሟል::

አንድ-ወጥ የሆነ የአካባቢ ጥበቃ ህግን ለመቅረጽ የተለያዩ የህግ ባለሙያዎችን የሠራተኛ ማህበራትን እንዲሁም ተማሪዎችን ያሰባሰበ አንድ ልዩ አለም አቀፍ የሥራ አውደ ጥናት ተደርጓል:: በተለይ ከጁን 1992 እስከ ጁን 1993 ባሉት ሰፊ ጊዜያት ውስጥ ይኸው ቡድንና ፋውንዴሽኑ በመተባበር አያሌ አሁጉራዊ ስብሰባዎችን በላቲንና በሰሜን አሜሪካ: በአረብ አገሮች: ከሰሃራ በታችና በምዕራብ አፍሪካ እንዲሁም በምስራቅ አውሮፓ:- በደቡባዊ እስያና በቻይና በሚገኙ ሀገሮች አካሂዶ በጋራ አፋጣኝ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚሹ ጉዳዮችን በማንሣት ከፍተኛ ውይይትና የሃሳብ ልውውጦችን በማድረግ አንድ የሆነ የጋራ ዓላማና ድንጋጌ እንዲነፀባረቅ ረድቷል:: በጠቅላላው ይህ ሂደት ያተኮረው ፈረንሳይ ውስጥ **"Les vaux de cernay"** ላይ ከመስከረም **27** እስከ **30,1993** ለተደረገው "የዓለም አቀፍ ጠቅላይ መንግሥታት" ስብሰባ መቅረብ የሚገባቸውን ጉዳዮች ወይም የመወያያ አጀንዳንና ድንጋጌዎችን ለማዘጋጀት ነበር:: በተጨማሪ ይህ የጋራ ድንጋጌ ሌላ **16** ከተለያዩ ሀገሮች የተውጣጡና የተለያዩ ዝንባሌ ያላቸውን እውቅ ግለሰቦች በጉዳዩ እንዲሳቡ አድርጓል:: ድንጋጌውንም ባስተላለፉበት ወቅት ብዙ አመለካከቶችንና ሃሳቦችን በማወዳደር አንድና የጋራ በሆነ ሃሳብ ላይ በመድረስ የጋራ የሆነ

የመወያያ መድረክ ለመፍጠር ተችሏል:: በመጨረሻም የውይይቱ ተሳታፊዎች አንዳንድ ገንቢ የማሻሻያ ሃሳቦችን እንዲያበረክቱ በመጋበዝ "የተባበረችና ሃላፊነት የሚሰማትን ዓለም ለመፍጠር የተወጠነ መድረክ" በሚል ውጤት ስብሰባው ተጠናቋል::

## የወደፊት እርምጃዎች

ከዓለም አቀፍ ጠቅላይ መንግሥታት ምሥረታ ውል ዝግጅት በኋላ አዲስና እውነተኛ የሆነች ዓለምን ለመመሥረት የሚደረገው ትግል ሊጀመር ጥረቱ ከተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የሚገኙትን ሰዎች በሙሉ የሚያሳትፍ ይሆናል:: ይህም ተሳትፎ የሚጀምረው ውሉን ከማዘጋጀት አንስቶ "ዓለም አቀፋዊ ጠቅላይ መንግሥታት" በተጨባጭ እስከ መመሥረት ይዘልቃል:: በተጨማሪም ይህ ተሳትፎ በጠቅላላው በምድራችን ላይ ያሉትን ህዝቦች በማስተባበር ለ21ኛው ክፍለ ዘመን አንድ የሆነ የወደፊት ተስፋ እንዲኖራቸው በሚያስችል መልኩ መቅረጽ ይሆናል:: ይህም ምሥረታ በ1994 እውን ይሆናል::

የሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ "የተባበረችና ሃላፊነት የሚሰማትን ዓለም ለመፍጠር የተወጠነውን መድረክ" ወደፊት እውን ለማድረግ ውሳኔያቸውን ያስተላለፉ ቡድኖችን በማህበር ማደራጀት ይሆናል:: እንዲያውም አንዳንድ

ቡድኖች ተሳታፊ ለመሆን ካስተላለፉት ውሳኔ ባሻገር የወደፊት ውጥኑን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማበርከት ይፈልጋሉ::

በመጨረሻም የተባበረችና ሃላፊነት የሚሰማትን ዓለም ለመፍጠር የሚደረጉት ትብብሮችን ማዕከል በማድረግ የዓለም አቀፍ ጠቅላይ መንግሥትን ለማቋቋም የወጡት ድንጋጌዎችና ውሎች መልክ ይይዛሉ::

ይህ ትብብር ወይም ማህበር ህጋዊ መዋቅር እንዲኖረው አልተስማማንም:: ምክንያቱም ትብብሩን የምንፈልገው ለጋራ ግባችን ስኬታማነት መስእዋትነት ለመክፈል ፍላጎቱ ያላቸውን ሰዎች ኃይልና ችሎታ በሰፊ ለማንቀሳቀስ ብቻ ስለሆነ ነው::

ፋውንዴሽን ፑር ለፕሮግረስ ዳለሆም በመጀመሪያ ጊዜ ማለትም 1986/1993 እንዳደረገው አሁንም በ1994/1999 ለሚደረገው ጥረት የበኩሉን ድጋፍ ይሰጣል:: ይሁን እንጂ የተያዙትን ፕሮጀክቶች መጠንና ዓይነት ግምት ውስጥ በማስገባት ሌላ የድጋፍ መንገድ ይፈልጋል::

# የተባበረችና ኃላፊነት የሚሰማትን ዓለም ለመፍጠር የተወጠነ መድረክ

የህብረተሰባችን አኗኗርና የልማቱ ዕድገት አቅጣጫ በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ወደፊት የሰው ልጅ ራሱን በራሱ ያጠፋል:: ይህ ደግሞ የማንቀበለው ነው:: ይሁን እንጂ ስጋቱን ለመከላከል ስር ነቀል የሆነ የአስተሳሰብና የኑሮ ዘይቤን መለወጥ አስፈላጊ ነው:: ለውጡንም ተግባራዊ ለማድረግ ከእያንዳንዳችን በፍላጎት ላይ የተመሠረተና የተቀናጀ ጥረትን ይጠይቃል:: የተቀናጀና የተጠናከረ የህዝቦችን ተግባር ለመፍጠር አስፈላጊና ዋና ዋና በሆኑ ጉዳዮች ስምምነት ላይ በመድረስ ችግሮቹን ለማጥፋት መንገድ መቀየሱ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው:: የተባበረችና ኃላፊነት የሚሰማትን ዓለም ለመፍጠር የራሳችንን ውሳኔ ስናደርግ ባንፃሩም ይህንን መድረክ በመጠቀም ወደፊት በአንድ ላይ ሆነን አዲስ የሆነች አለም ለመገንባት ነው::

ዓለማችን እንግዳና ብቸኛ የሆኑ ብዙ ልዩነቶች ያሉባት ብትሆንም የምናወጣቸው ትልሞች (እቅዶች) እነዚህን ልዩነቶች አጥፍተው ፍላጎታችንና ህልውናችንን ለማረጋገጥ የሚያስችሉን መሆን ይገባቸዋል::

እንደመድረኩ አባባል ትኩረት ሊሰጥበት የሚያሻው ጉዳይ ከሀገር ሀገር ከአህጉር አህጉር ቢለያይም ቅሉ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያለንን ስምምነት ሊሸረው አይችልም::

## I. ያሉት ችግሮችን ጠቋሚዎች

ዛሬ በዓለማችን መሠረታዊ ያልተማሉ ፍላጎቶች እስካሁን መልስ አላገኙም:: እየባከኑና እየወደሙ ያሉት የሀብት ምንጮች በሥራ ላይ ሊውሉ ካልቻሉ ከሥራና ከፈጠራ ጥረቶች ጋር ያልተጣጣሙ ይሆናሉ:: ይህ ሁኔታ የማንቀበለው እና የማያዋጣ ነው::

በሶስት ዋና ዋና የአለመመጣጠን ችግሮች ውስጥ ወድቀናል:- ማለትም በበለፀጉና ኃላቀር በሆኑ አገሮች:- በህብረተሰቡ ውስጥ ባለው ሃብትና ድህነት እንዲሁም በሰው ልጅ እና በተፈጥሮ:: እነዚህ ባለሶስት ፈርጅ ያለመመጣጠን ችግሮች በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ግንኙነቶች በተጨማሪም በህብረተሰቡና በአካባቢው ያሉትን ችግሮች አጉልቶ ያሳያሉ:: እነዚህ ችግሮች ማለትም በህብረተሰቡና በአካባቢው ያለው መቀራረብ ከወንድና ከሴት መቀራረብ ተነጥሎ ሊታይ አይገባም::

በማንኛውም ደረጃ እነዚህን ባለሶስት ፈርጅ ችግሮችን በተናጠል ለማስወገድ አዳጋች ነው:: ምክንያቱም በሰው ልጅና በአካባቢው ያለውን ችግር ለማስወገድ ስንጥር በተጓዳኝ መልኩ በሰዎች መካከል ያለውን ያለመግባባት አጥፍቶ ስምምነትን ለመፍጠር ካልተቻለ አስቸጋሪ ይሆናልና::

በእርግጥ ከላይ ያነሣናቸው ችግሮች ምንጭ አንድ ነው:: ላለፉት ሁለት ምዕተ ዓመታት ዓለማችን ከፍተኛ ለውጦችና ዕድገቶችን አስመዝግባለች:: ከምዕራቡ ዓለም የተገኙት አዳዲስ ግኝቶች በአራቱም ማዕዘናት ተሰራጭተዋል:: ነገር ግን ብዛት ያላቸው ሀገሮች በመንፈሳዊና በሞራል ውድቀት ችግር ውስጥ ተዘፍቀዋል:: በሌላ በኩል የተገኙትን አዳዲስ ስልጣኔዎችን:- ያሉብንን ችግሮች ተመካክረንና ተደጋግፈን ለሰው ልጆች ጥቅም ልናውላቸው አልቻልንም:: እንዲያውም የእነዚህ ችግሮች መንስዔ በአሁኑ ጊዜ ያሉት የሳይንስና የቴክኖሎጂ እድገት ውጤቶች መሆናቸው አሌ የሚባል አይደለም:: የሳይንስና የቴክኖሎጂው እድገት የፈጠረው ከፍተኛ የሥራ ክፍፍልና የገበያ መበራከት ያሉትን ችግሮች ወደጎን በመተው ቅጥ ባጣ የገንዘብ ማካበት ላይ ያተኮረ ሆነ::

አንዳንዶች በአጭሩ ሲያስቀምጡት ከወቅቱ ችግሮቻችን መንስዔዎች ዋንኛው በምእራቡ ዓለም የሚደረገው ገደብ የለሽ የኃብት ማግበስበስ ውጤት ነው ይላሉ::

ስልጣኔ እናራምዳለን በሚሉት አስተሳሰብ የስልጣኔ መሠረቶች የነጻ ንግድ ልውውጥና ሳይንስ ለሰው ልጆች እድገት ፀጋ ሰላም ደስታ እንዲሁም ነጻነት ዋስትና ናቸው ይባላል:: ነገር ግን እነዚህ ሁኔታዎች በተገባቢጦሽ የሰውን ልጅ ወደ ድህነት ጦርነት ጭቆናና ሰላም መደፍረስ በአጠቃላይ ከላይ የጠቀስናቸው ችግሮች ሁሉ መንስኤ ሆነው እናገኛቸዋለን::

ላለፉት ጥቂት ምዕተ ዓመታት የምዕራቡ ሥልጣኔ በተቀሩት የዓለም ክፍሎች የተለያዩ ችግሮችን እየተወ አልፍዋል:: ለመግለጽ ቢያስፈልግ ቅኝ አገዛዝ ከዚያም ለጥቆ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የብዝበዛ መረባቸውን በመጣል ወይም በመዘርጋት የቀረው የዓለም ክፍል በራሱ ፍላጎትና ከራሱ በመነጨ የእድገት ጎዳና እንዳይጓዝ በማድረግ ይቅር የማይባል ግፍና በደል ፈጽመዋል::

በአንጻሩ የሰውን ልጅ እድገትና ልማት ከግብ ማድረሻ መሣሪያዎች ናቸው የተባለላቸው ሁለቱ የሥልጣኔ መሠረቶች ማለትም ነጻ የንግድ ልውውጥ ሥርዓትና ሳይንስ በእንጥልጥል ላይ ያሉትን የዓላማችን ችግሮችን ወደ ጎን በመተው ዛሬ በራሳቸው ግብ ሆነዋል።

እንደ ምጣኔ ሃብት ተመራማሪዎች አባባል የሸቀጦች ወይም የገንዘብ የልውውጥ ስርዓት በበለጠ ነጻ እየሆነ በሄደ ቁጥር በሰው ልጆች ላይ ለተደቀኑት ችግሮች መፍትሄ ሊሆን እንደሚችል አፋቸውን ሞልተው ይናገራሉ። ቁም ነገሩ ግን ሌላ ነው። ሳይንስ እንደሚታወቀው ተፈጥሮን ለመረዳት እንዲሁም ማንኛውንም ክስተቶች ለማወቅና ለፈጠራ የምንጠቀምበት ቢሆንም ዛሬ ግን ያለንን ሳይንሳዊ እውቀት በማስተባበር የሚጠቅሙንና የሚጎዱንን መሣሪያዎች ለመሥራት እየተጠቀምንባቸው ነው።

ገበያዎች በራሳቸው መንገድ እየተመሩ አንዱ የአንዱንና አንዱ የሌላውን ፍላጎት ለማርካት ሲራወጡ ይታያሉ። ነገር ግን ምንም ጊዜ ቢሆን የአብዛኛውን ሕዝብ ያልተሟሉ መሠረታዊ ፍላጎቶችን የአካባቢ መበከልን አደጋ በተጨማሪም የወደፊቱን ትውልድ የመኖር ፍላጎቶች በበቂ ሁኔታ ለሟሟላት ለአንድም ሴኮንድ እንኳ ሲጥሩ አልተስተዋሉም። ገበያና ሳይንስ

በአጠቃላይ ብዙ ጥቅምና ገንቢ ሚና የሚጫወቱት በህብረተሰቡ ፍላጎትና ምርጫ እንዲሁም በእድገትና ልማት ላይ የተመሠረተ ዓላማ ሲኖራቸው ብቻ ነው::

ይሁን እንጂ በሳይንስና በገበያ መካከል ከፍተኛ የአላማ ግጭት አለ:: ይህ ደግሞ ያለውን ችግር በከፍተኛ ሁኔታ ያባብሰዋል:: በአንጻሩ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ እድገቶች ያስከተሉትን በህዝብና በግዑዝ አካላት ወይም በተፈጥሮ ላይ ያላቸውን የበላይነት ስንመለከት የሰው ልጆች ለመጪው አለም ያላቸው ብሩህ ተስፋ ህብረትና የዓላማ አንድነት በሳይንስና በቴክኖሎጂ ጎጂና ያልተገደበ ዕድገት ደብዝዟል:: ሳይንስና ቴክኖሎጂ በሰዎችና በሰዎች ከዚያም በሰዎችና በአካባቢያቸው ያለውን ትስስር አድክሞታል:: ይኸውም ገደብ ያጣ እድገት በስብዕናና በተፈጥሮ ላይ ከባድ ተጽዕኖ አሳድራል:: ይህም አጠቃላይ ማህበራዊና ተፈጥሮአዊ ቀውስን ለመፍጠር የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል::

ዛሬ የሰው ልጅ የማወቅና የመመራመር ፍላጎቱ ተዳክሞ ትኩረቱ ሥልጣንና ገንዘብ በማካበት ላይ ሆኗል:: እንዲያውም የሰዎች ስኬታማነት የሚለካው ባግበሰበሱት የኃብት መጠን ነው:: በአሁኑ ወቅት መንፈሣዊው ዓለም ተረስቶ ሕዝቦች ለቁሳዊው ዓለም ደስታ ከዚህ እዛ ሲራወጡ ይታያሉ:: ይህንን ሁኔታ በመቀየርና ፍላጎታችንን ቀስ በቀስ ለሚሟላት የትኩረት

አቅጣጫችንን በመቀየር ያለንን ኃይልና እውቀት በመጠቀም የረጅምና አጭር ጊዜ ትልሞቻችንን ሊያሳኩ ወደሚያስችሉ ደረጃዎች ላይ መድረስ ስንችል ብቻ ነው:: ያለዚያ ውጤቱ በብዙ ህብረተሰብ ውስጥ እንደሚታየው የስነምግባር ቀውስ የሥልጣን መባለግ የእጾች ሱሰኝነት መበራከት ስለ ሌሎች እንዲሁም ስለ አካባቢያችን አለመጨነቅ በአጠቃላይ በዘመናችን ጎልቶ የሚታየው የወጣቱ ትውልድ ግራ መጋባትን ያስከትላል::

በአሁኑ ዘመን ከላይ የተገለጹት ባለ ሶስት ፈርጅ ችግሮች የዚሁ ክስተት ውጤት ናቸው:: በግልጽ እንደሚታየው የሳይንስና የገበያ መሥፋፋት የራሳቸው የሆኑ ጎጂ ጎኖች አሉዋቸው:: ስር የሰደደ የኑሮ ደረጃ ልዩነት ስግብግብነትና አርቆ ማሰብ የጎደለው ህብረተሰብ እንዲፈጠር የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋልና:: በተጨማሪም ዓለማችን በፍጥነት እየተቀየረች ነው:: የሰውም ልጅ በተፈጥሮ ላይ ያለው ተጽዕኖም በዛው ልክ አድጓል:: ዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ መጠንም ጨምሯል::

ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት የሰው ልጅ ሥራውን የሚተገብርባቸው ሥርዓቶች አሁንም እንዳሉ ናቸው:: በማንኛውም መስክ እነዚህ አፋጣኝ ምላሽ የሚጠይቁትን የምድራችን አበይት ችግሮች በባህላዊም ሆነ በዲሞክራሲ ላይ የተመሠረቱት ተቋሞች መልስ የሚያገኙላቸው አይደሉም:: ነገር ግን እነዚህ

ተቋሞች ኃላፊነቱን ወስደው በዓለማቀፍ ደረጃ ለችግሩ መፍትሄ መሻት ይኖርባቸዋል:: ይሁን እንጂ እስካሁን ይህን ከፍተኛ ኃላፊነት የወሰደ አካል የለም:: ሁሉም የሰው ልጆች የመጨረሻ ግብ አላቸው:: ከግባቸው መድረሻ መንገድና ዘዴ በጃቸው ነው:: ግን ይህን ለማድረግ ተስኖአቸዋል::

አለማችን ባልተጠበቀና ፈጣን በሆነው የለውጥ ሂደት ምክንያት ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ተዘፍቃለች:: ይኸውም የተትረፈረፈ የምርት ክምችት ፈጣን በሆነ የሕዝብ ብዛት የምርት ፍላጎት መጨመር ሲሆኑ በተጨማሪ የመረጃ ወይም የኢንፎርሜሽን እና የመዕዋለ ንዋይ ልውውጥ በጣም የተራቀቁና ከፍተኛ ኃይል የሚጠይቁ ዘዴዎችን መጠቀም ብዛት ያላቸው ጥሪቶችን መጠቀም እንዲሁም በከፍተኛ ደረጃ የፋብሪካ ቅሪቶችን በየቦታው መቅበርና መጣል በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው የኑሮ ደረጃ ልዩነት ማደግ ሲሆኑ በእነዚሁ ምክንያቶች መሬትና የሚኖርባት ሕዝብ ፍላጎት ባለመጣጣማቸው የመጪውን ትውልድ ዕድልና ህይወት ስጋት ላይ ጥሎታል::

አሁንም እያንዳንዱ የሕብረተሰብ ክፍል ትኩረት የራሱ የሆኑትን ጥቅምና አላማ ከዳር ለማድረስ መታገልና የበለጸገው የሕብረተሰብ ክፍል ያለበትን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና ያጋጠሙትን ከፍተኛ የሥራ አጥነትን ሁኔታ መዋጋት ነው:: በስልጣኔ ኋላቀር የሆነው ደግሞ የሰለጠኑትና በሳይንስና

ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ ለመድረስ ሲል ብቻ ወደር የሌለው የሥራ ኃይሉንና የተፈጥሮ አካባቢውን መሥዕዋት ያደርጋል:: በእርግጥ የየሕብረተሰቡ ጥያቄዎች አግባብነት ያላቸውና አንዱ ከአንዱ የሚነጣጠሉ አይደሉም:: ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድ እነዚሁ ሁኔታዎች ራሳቸው በሕብረተሰቡ ውስጥ የኑሮ ደረጃ ልዩነት እያደገ እንዲመጣና እያደር የሰው ልጅ በኃብትና በድህነት ላይ የተመሠረተ ጭቅናና ብዝበዛ እንዲሁም ሥር የሰደደ የአካባቢ አየር ንብረት አለመመጣጠን ያስከትልና ያው የመጨረሻው የችግሩ ገፈት ቀማሽ ድሃው የአለማችን ጥቁር ሕዝብ ይሆናል ማለት ነው::

እስካሁን የተደረጉ ጥናቶች አንድና የጋራ ሃሳብ ላይ ያላቸው ስምምነት እንደሚያስረዱት ያጋጠሙንን ችግሮች ለማስወገድ አሁን በያዝናቸው በ1990ዎቹ ውስጥ ውሳኔ ላይ ተደርሶ ውሳኔዎቹም በተግባር ካልተተረጎሙ አሁን ያለው የአለመመጣጠን ችግር በሚመጣው ግማሽ ምዕተ ዓመት የሰውን ልጅ ከአሁኑ የከረረና አስከፊነቱ የባሰ ችግርና መከራ እንዲጋረጥበት ያደርጋል:: ስለዚህ እንደኛ እምነት የሰው ልጅ ዛሬ ነገ ሣይል ይህን ፊቱ ላይ የተደቀነውን ችግር ለማስወገድ መንፈሣዊ ስነ-ምግባራዊ ምሁራዊና ማህበራዊ ለውጦችን በከፍተኛ ሁኔታ ለመጀመር ዝግጅት ማድረግ ይገባዋል:: ይኽንን እቅዱን ከዳር ለማድረስ አስፈላጊውን የተግባር መመሪያም የማውጣት ኃላፊነት አለበት::

## የተባበረችና ኃላፊነት የሚሰማትን ዓለም ለመፍጠር የወጣ የጋራ መመሪያ

እኛ እንደምንለው አሁን ያለው ሁኔታ ምንም አስከፊ ባይሆንም የችግሩ ውስብስብነት የሰፈነው የስጋት ውጥረት ለችግሩ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ይገፋፋናል፡፡ የወደፊት እጣውንና ኑሮውን ለማሳካት የሚጥር ህብረተሰብ የተለያዩ መመሪያዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡ ምክንያቱም ምርጫውንና ውሣኔውን ለማስተላለፍ፡፡ በዓለም ላይ ያሉትን የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ባህልና ልማድ ከግምት ውስጥ በማስገባት አሁን ላለንበት ጊዜ ዋናና ጠቃሚ በመሆናቸው እምነን ከዚህ በታች የሚከተሉትን መመሪያዎች አውጥተናል፡፡

### 1. የመከላከያ መመሪያ

ይህችን ምድር ከእናት አባቶቻችን እንደወረስን ሁሉ እኛም ለመጪው ትውልድ የማስተላለፍ ግዴታም ኃላፊነትም አለብን፡፡ ማናችንም ቢሆን በተፈጥሮው ሃብቷ የታደለ ቦታ ብንወለድም ችሎታችንን ተጠቅመን የዚችን ምድር ሃብትና ጥሪት በማን አለብኝነት ልናባክንና ልናወድም አንችልም፡፡ ምንም እንኳ ያለን የሳይንስና የቴክኖሎጂ እድገት እንደፈለግን እንድንሆን ቢያደርገንም ይህ ነፃነት የተፈጥሮን ሚዛን ሳይጸረር ጎን ለጎን እንዲካሄድና

በተጨማሪም አስፈላጊ የሆኑትን እንደ ውሃ አየር አፈር ባህሮችና ውቅያኖሶችን እንዲሁም ማንኛውንም ሕይወት ያለውን ፍጡር ከተፈጥሮ ጋር በስምምነት ማቆየት ይገባል:: እንዲሁም የሰው ልጅ የወደፊት የዕድገት አቅጣጫ ወይም ጉዞ ምርቱንና የአኗኗር ዘይቤውን ያለውን ሃብት በሚያባክንና የአካባቢ አየር ሚዛን የሚጎዳ መሆን የለበትም::

## 2. የሰው ልጅ መመሪያ

ማንኛውም የሰው ፍጡር ለመኖር አስፈላጊ የሆኑትን ማለትም ሰው በሰውነቱ ተከብሮ መኖርን እኩልነትን እንዲሁም ጠንካራ የሆነ የእርስ በርስ ስምምነትን ፈጥሮና አጠንክሮ መኖር እንደሚችል እንዲሁም ለተፈጥሮና በአጠቃላይ ለፍጡራንና ለተፈጥሮ ከፍተኛ ግምትና ክብርን ማረጋገጥ ይገባዋል::

## 3. የኃላፊነት መመሪያዎች

ማንኛውም ግለሰብ ድርጅት መንግሥት እንዲሁም አለማቀፋዊ ድርጅቶች በሰዎች መካከልና በተፈጥሮ መካከል መግባባትን ለመፍጠር አቅማቸው የፈቀደውን ሃይልና ሃብት እንዲያበረክቱ ያሳስባል::

## 4. የብክነት ማስተካከያ መመሪያዎች

ቅጥ ያጣ የጥቅም ወዳድነታችንን መቆጣጠር በይበልጥ መማር ይኖርብናል:: ገንዘብንና ሀብትን በመርጨትና በማባከን አዙሪት የተዘፈቁ ባለፀጎች የኑሮ ዘይቤዎቻቸውን የማሻሻል ለውጥ በማድረግ ፍጆታቸውን ማስተካከል ይገባቸዋል::

## 5. የጨዋነት መመሪያዎች

የሰው ልጅ ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማምረት የሚጠቀምባቸውን የአመራረት ሥልቶችና ቴክኒኮች በተፈጥሮ ላይ ተጽዕኖ ወይም ጉዳት የሚያደርሱ መሆን የለባቸውም::

## 6. የልዩነቶች መመሪያ

ያሉትን የባሕል ልዩነቶች አውቆ ልዩነቶቹን በአግባቡ መያዝ የማንኛውም ሕብረተሰብ ኃላፊነት ነው:: ያለውም የሥልጣኔ ደረጃ ልዩነት ራሱ በራሱ አሁን የሚታዩትን የተለያዩ ችግሮች ማለትም በአካባቢና በሰዎች መካከል ላሉት ችግሮች ምክንያት ናቸው:: ያለውን ከፍተኛ የተፈጥሮ ሃብት

መንከባከብም አስፈላጊ ነው:: እስካሁንም ያለውን የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ላደረጉ ወይም ለሚያደርጉ ማህበረሰቦች ከፍተኛ አድናቆትና ክብር ሊነፈጋቸው አይገባም::

### 7. የዜግነት መመሪያ

ማንኛውም የሰው ፍጡር የማህበረሰቡ አባል መሆኑን ማረጋገጥና ብሎም በሰውነቱ ክብር ሊነፈገው እንደማይገባ ማወቅ:: በተጨማሪም ዓለማችንን በቀላሉ ለግል ፍላጎትና ገበያቸው ማርኪያ መንገድ ወይም መሣሪያ አድርገው ለሚጠቀሙ ሰዎች ከላይ ከ1-6 የጠቀስናቸውን ኃላፊነትና አስፈላጊ መመሪያዎች በግልፅ በማስረዳት የዕለት ተዕለት ስራቸው መመሪያ እንዲያደርጓቸው መጣር ናቸው::

## III. የትልሞቻችን የሥራ መመሪያ

### 1. የአለማቀፋዊ ትልም አስፈላጊነት

የሰው ልጅ እነዚህ ሦስት ችግሮች ከፊቱ ቢጋረጡም እስካሁን ችግሮቹን ለማስወገድ ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል:: ከአካባቢ እስከ ከተማ ከከተማ እስከ

ሀገር ከሀገር እስከ ዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውሎችና ስምምነቶች ተደርገዋል:: በተጨማሪም በተናጠል በአንዳንድ ሀገሮች ለችግሮች ትኩረት በመስጠት የኃይል አጠቃቀም ፖሊሲያቸውን በማሻሻል ገንቢ እርምጃ በመውሰድ የበኩላቸውን ድርሻ እያበረከቱ ነው:: ነገር ግን ይህ የተናጠል እንቅስቃሴ እየተባባሰ የሚመጣውን የዓለማችንን ችግር ሙሉ ለሙሉ ለመፍታት በቂ አይደለም::

በአሁኑ ጊዜ ትልቅ የሆነ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ይታያል:: በአንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች በተናጠል ችግሮቹን ለማጥፋት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችና ያሉት ችግሮች ሲታዩ በጣም የማይመጣጠኑ ናቸው:: እያንዳንዱ ሰው ድርጅትና ሀገር ያላቸው ችግሮች ፋታ ሊሰጣቸው እንደማይገባ ጠንቅቀው ቢያውቁም ችግሮቹን በተጨባጭ ለማስወገድ እስካሁን የታየ የተባበረና የጠነከረ ተግባራዊ ጅምር በየትኛውም ቦታ አልታየም:: ስለዚህ አሁን ያለን አማራጭ ያለውን የቴክኖሎጂና የገበያን ዕድገት በማጣመር ላሉት ችግሮች መፍትሄ እንዲሆኑ መጣር ነው:: ምክንያቱም እስካሁን ያለፍንባቸው በአይዲዮሎጂ ላይ የተመሠረቱ ህዝባዊ ተቋሞች ምንም ምላሽ ሊሰጡን አልቻሉም:: ስለዚህ በሚታዩት ችግሮች ሳንደናገጥ የጋራ ፍላጎታችንና

ጥቅሞቻችንን ለመጠበቅ አስፈላጊውን አመቺ የወደፊት መርሆቻችንን በመንደፍ የተጠናከረና የተቀናጀ የሥራ መመሪያ በማውጣት ያሉትንና ወደፊትም ሊገጥሙን የሚችሉትን ችግሮች ለመከላከል ከወዲሁ ኃላፊነታችንን መወጣት አለብን።

ቀጣይነት ያለውና የተፈጥሮን ሚዛን የሚጠብቅ እድገት እናሳያለን የሚል ግምት የለንም። በተጨማሪም እያደገ በመጣው ቴክኖሎጂ ችግሮቹን ለማጥፋት በመደረግ ላይ ያለውም ጥረት ሙሉ በሙሉ ተስፋ የሚሰጠን አይደለም። ልንገነዘበው የሚገባው ነገር ቢኖር የምንወስዳቸዉ እርምጃዎቹ የግድ በሰዉ ልጆች እንዲሁም በአካባቢያቸዉ የተመጣጠነ ግንኙነት ሊፈጥሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው። አላማዎቻችንም አሁን ያሉትን ችግሮች የሚያባብሱ ሳይሆኑ መፍትሄ ሠጪ መሆን አለባቸዉ። በአጠቃላይ ከላይ የጠቀስናቸዉን 7 መመሪያዎች ከተግባሮቻችን ጋር በማጣጣም የወደፊት ትልሞቻችንን ተግባራዊ ለማድረግ መጣጣር ይኖርብናል። ይኽ ደግሞ ኃላፊነት የሚሰማትንና የተባባረች ዓለም ለመፍጠር ከፍተኛ ፍላጎት ስላለን ብቻ ነዉ።

ይኽን ዓላማችንን ከዳር ለማድረስ ያለንን የሰዉ ኃይልና ሃብት ማስተባበር አለብን። ይኽንንም ለማድረግ እንችላለን። ለምሣሌ ከታሪክ እንደምንረዳዉ በ1930 ዓ ም በምዕራቡ ዓለም የደረሰዉ የኤኮኖሚ ቀዉስ እንዲሁም በዚህ ችግር ምክንያት የሁለተኛዉን ዓለም ጦርነት ለመወጣት

የተደረገዉን የሰዉና የገንዘብ ኃይል ርብርቦሽ ማስታወሱ ብቻ ማስረጃ ሊሆነን ይገባል:: ስለዚህ አሁን በመገባደድ ላይ በሚገኘዉ ምዕተ ዓመት የሚታዩትን ችግሮች ማለትም ድህነትን ለመዋጋት ያሉንን የቴክኖሎጂ

የሃብት ምንጮችና የሰዉ ኃይል በማስተባበር አሁን ተጋርጦብን ያለዉን የምድራችንን የተፈጥሮ ሚዛን ከጉዳት መጠበቅ አለብን::

ዛሬ 20% የሚሆነዉ የዓላማችን ህዝብ 80% የሚሆነዉ የአላማችን ኃብት ባለቤት ሲሆን ጥቂት የቤተሰብ ክፍሎች የሚያገኙት ገቢ ደግሞ ሲመዘን ብዙ ሺህ የተቸገሩ ቤተሰቦችን ሊያስተዳድር የሚችል ነው:: ስለዚህ ከፍተኛ ገቢና ኃብት ያላቸው ቤተሰቦችና ሀገሮች ያሉትን ችግሮች ለማስወገድ በሚደረገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይጠበቅባቸዋል::

ይኸ ሃሳብ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ካገኘ ሀገሮች አንድነታቸውን በማጠናከር የጋራ ከሆነ የፖለቲካ መሠረት ላይ በመነሳት የወል አላማና ግብ መወጠን ይጠበቅባቸዋል:: ይህ ሁኔታ በአንፃሩ ተጨባጭ የሆነ የሰዎች አንድነት መኖሩን ያስገነዝበናል:: በአጠቃላይ·በሰዎች መካከል የጋራ የሆነ የዓላማ አንድነት የመፈጠሪያ መንገድና ወደፊት የተጠናከረ ዓለም አቀፍ

ትብብርና ግንኙነት ለማሳደግ ይረዳል:: ከጊዜ ወደጊዜ ያለን ቁርጠኛ አቋም እየጠነከረ እንዲመጣና ከግብ ለመድረስ የተጠናከረና የተሟላ ድርጅታዊ መሪ ደንብና የቴክኖሎጂ እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው::

## 2. ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ አንድነትና ልዩነቶች

በቅድሚያ ዓለማቀፋዊ መፍትሄ ወይም ምላሽ ሊሰጥባቸው የሚሹትን እነዚህን ሶስት የዓለማችን ችግሮች የጋራ የሆኑትን ፍላጎቶቻችንን ከዳር እስከዳር በማሰራጨትና በመገንባት በሰዎችና በህብረተሰቡ መካከል ያለውን ልዩነት እንዲሁም ለህይወት አስፈላጊ የሆኑትን በመጠበቅና በመንከባከብ በሰውና በተፈጥሮ ሚዛን መካከል አዲስ የሆነ ግንኙነትን በማሳደግ ያለንን ኃይልና የምግብ ክምችት በማሳደግ በተጨማሪም ከላይ የጠቀስናቸው በጋራ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚሹ ጉዳዮች ወደፊት አንድ-ወጥ ተግባራዊ መፍትሄ ለማምራት ያዘጋጀናል::

ከዚህ ባሻገር እያንዳንዱ የዓለም ክፍል የደረሰበትን የእድገት የታሪክ እንዲሁም የሚገኝበትን የአየር ንብረት ክልል ግምት ውስጥ በማስገባት በተናጠል በቅድሚያ ትኩረት የሚጠይቁ ጉዳዮችን ለማስወገድ መንገድ መቀየሱ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም:: በተለይ የበለፀጉ አገሮች

የተጋረጡባቸውን አዳዲስ ችግሮች ለማስወገድ ስር-ነቀል የአኗኗር ዘይቤ ሊቀይሱ ይገባል:: ለምሣሌ በቀድሞ ሶቪየት ህብረት ስር የነበሩ አገሮች ውስጥ በስፋት ተንሰራፍተው የምናያቸው የሥራ አጥነት ችግር እንዲሁም አጥጋቢና ተስማሚ ያልሆነ የአመራረት ስልቶችንና አስጊ የሆኑ የወታደራዊና የሲቪል የኑክለር ኃይል አጠቃቀም ያስከተለው የአካባቢ ብክለትና የመሳሰሉት ከፍተኛ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው:: በኢንዱስትሪ ያደጉት አገሮች ውስጥ ደግሞ የሚታየው ያለውን የተፈጥሮ ሃብትና የሰው ሃይል ያለአግባብ መጠቀም ነው:: በአንፃሩም ድሃ በሆኑት የዓለማችን ክፍሎች መጀመሪያ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ደግሞ የሕዝብን ብዛት እድገት መቆጣጠርና ስር የሰደደውን ችግር ማስወገድ ሲሆን በተጨማሪም ያለውን የውሃና የአፈር ሃብት ከራሳቸው በፈለቀ ሳይንስና ቴክኖሎጂ በመቆጣጠር መግታት ናቸው:: በረሃማ በሆኑት አገሮችም እንዲሁ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች የውኃ ኃብታቸውን በማስፋፋት አካባቢያቸውን በዕፀዋት ለመሸፈን የሞት ሽረት ትግል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: በጠቅላላው በምድራችን መጠነኛ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸው ደግሞ ያሉትን ባህሮች ውቅያኖሶች እንዲሁም የኦዞን ሽፋንን (የአካባቢ አየርን ከመሟሟት መጠበቅ) ሲሆን እንዲሁም አየሩን ሊበክሉ የሚችሉ የጋዝ ጭሶችን ማስወገድ ይሆናል:: ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ምላሽ መስጠትና በጋራና በተናጠል ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መቀበል በራሱ ዓለማችን በልዩነቶችና በአንድነቶች

የተመሠረተች መሆኗን ያስገነዝበናል:: ከዚህም ባሻገር የተናጠል እርምጃ እንዳንወስድ ይረዳናል:: ስለዚህ ህብረታችንን በማቀናጀትና በማደራጀት ባለብዙ ፈርጅ ትልም መቀየስ አስፈላጊ ነው::

## 3. የጥምር ተግባራዊ እርምጃ ደረጃዎች

በሁሉም ደረጃ አሁን የተጋረጡብንን ችግሮች ለማስወገድ የማያወላውል ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ ይኖርብናል:: እያንዳንዱን ግለሰብና ዜጋ እንዲሁም ተገልጋዩን በተመለከተ አሁን ስለአለው ሁኔታ ያለውን እውቀትና መረጃ በማሳደግ አዲስ የሆነ የሥነ ምግባር ለውጥ በማድረግ ወደፊት ለምንያያዘው ገንቢ እርምጃ የበኩላቸውን ድጋፍና ጥረት በአካባቢ እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ዕድል መስጠት ከድርጅቶች ከባለስልጣኖች ከአካባቢ ተመራጮች ከፍተኛ የሆነ ኃላፊነት ይጠበቃል:: ይህንን ለመወጣት ኃላፊዎቻቸውንና አስተዳደራቸውን: ያላቸውን የሥራ ኃይልና ደንበኞችን በማስተባበር የሚያስተዳድሩት ሕዝብንም ለተግባር የሚያነሳሳ ሕግና ደንብ በማውጣት ለተግባራዊ ሂደቱ መሣካት የበኩላቸውን ድርሻ ማበርከት አለባቸው::

ከዚህ ሁኔታ በስተጀርባ አንዳንድ ሊተኮርባቸው የሚገቡና በጎ የሆነ ድርሻ ሊያበረክቱ የሚችሉ ጉዳዮች አሉ:: እነሱም በጥንት ጊዜ የነበሩት ማህበረሰቦች:- መንደሮች:- የገጠር ስፍራዎች:- የወል አካባቢዎች:- ከተሞችና የመሬት አቀማመጥ በአጠቃላይ ታሪካዊ መስኮች ሊያበረክቱት የሚገባ ድርሻ አለ:: ስለዙህም በመካከላችን ያሉትን የባህል: የማህበራዊ እና የተፈጥሮ ልዩነቶች ግምት ማስገባት ተገቢ ነው::

ባለፉት ምዕተ ዓመታት እንደሚታወቀው ከፍተኛ የሆኑ ውህደቶችን ለመፍጠር የሚወጡት ደንቦችና ስርአቶች የሚተገበሩት በመንግሥት ደረጃ ነበር:: እንዲሁም ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ልውውጦች መልክ የሚይዙት በጊዜው ባሉት ተጨባጭ ሁኔታዎች በመንተራስ ነበር:: አንዳንድ የአካባቢ አደጋዎችም በሚከሰቱበት ወቅት ለመከላከል የሚወሰዱት እርምጃዎች መንግሥታት በሚያስተዳድሩት ክልል ብቻ የተወሰነና ያላቸውን የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የራሳቸው የሆነ የእድገት ሞዴል በማውጣት ችግሮቻቸውን ለማስወገድና ለመቆጣጠር የተለያየ ትልም ይነድፉሉ:: አሁንም ይህ አይነቱ የመንግስታት እርምጃ የሚበረታታ ነው:: ስለዚህ ከላይ በአለማቀፍ ደረጃ አንዳንድ መረጃዎችን መለዋወጥ አስፈላጊ ነው::

ምንም እንካ ሰዎች እያደገ የመጣ ነጻነት ቢኖራቸውም በግላቸው የሚወስዱቸው እርምጃዎች ያለውን የተፈጥሮ ሚዛን የመጠበቅ ኃላፊነትን እንዲወጡ እገዛ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን አሁንም የአገሮች ሉአላዊነትና የድንበር ክልል የሚለው ፅንሰ ሃሳብ መሰናከል የሚፈጥር ነው፡፡ በርግጥ ይህን ባለሁለት ፈርጅ መሰናከል ለመለወጥም በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ወደፊትም መንግሥታት ከላይ ከተጠቀሱት ኃላፊነታቸው በተጨማሪ ዋና ዋና የፖለቲካ ውሣኔዎች የማድረግ እንዲሁም አንድነታቸውን ማጠናከሪያ ህግ ማውጣትና ቀረጥ የመቆጣጠር ሥልጣናቸውን እንደያዙ የሚቀጥሉ ሲሆን ይህንን ኃላፊነታቸውን በመረዳት የድርሻቸውን ለመወጣት ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ክፍሎች ጋር በመጣመር ራሳቸውን ልክ እንደ አንድ የአስተዳደር ደረጃ በመቁጠር የተባበረችና ኃላፊነት የሚሰማትን አለማችንን ለመመስረት ለሚደረገው ርብርቦሽ ከፍተኛ እገዛ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በእርግጥ የሚመጡት ዓመታት በተለያየ ደረጃ በየአህጉሩ የሚደረጉ ጥረቶች መጎልበት አለባቸው፡፡ በሀገሮችና መንግሥታት መካከል ብዙ ልዩነቶችና አለመመጣጠን ስላሉ ግልጽና ውጤታማ የሆኑ ውይይቶችን በዓለማቀፍ ደረጃ በማካሄድ አንድ የተቀናጀ ስልት በመቀየስ ያለውን ችግር መፍታት ሌላው አማራጭ ነው፡፡

እስካሁን በአንዳንድ አህጉራዊ ድርጅቶች የሚያበረታቱ ጅምሮች ታይተዋል:: ወደፊትም እንደነዚህ አይነቶቹ አህጉራዊ ድርጅቶች እያደጉ የሚመጡበት መንገድ ተመቻችቷል:: ነገር ግን የአደራጃጀታቸውና የመዋቅራቸው አይነት በተመሠረቱበት (ዓላማ) ጉዳይ ላይ የተወሰኑ ቢሆንም እስካሁን ከስምንት (8) እስከ አሥር (10)የሚደርሱ ድርጅቶች ተመሥርተዋል::

አሁን በተያያዝነው የ 21ኛው ክፍለ ዘመን ልክ ከ5 ክፍለ ዘመናት ጀምሮ የአንድ አገር መንግሥት እንደሚያደርገው ወደፊት እነዚህ ድርጅቶች በአባል ሀገሮች መካከል ያለውን የገበያ ሁኔታ እንዲሁም ከቀረው ዓለም ክፍል ጋር ያላቸውን የንግድ ግንኙነት በማሳደግ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ይገመታል:: እንዲያውም ይህን ሁኔታ በሰፋት ስንመለከተው በሰዎች መካከልና በሰዎችና በተፈጥሮ መካከል ያለውን ግንኙነት ደንብና ሥርዓት ለማስያዝ አመቺ ደረጃ ሲሆን ብሎም በዚህ ረገድ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት የሚችል የበታችና የበላይ የሌለበትን ዓለማቀፋዊ መስተዳድር ለመመሥረት መንገድ ይከፍታል:: እነዚህ አህጉራዊ ድርጅቶች የፀጥታን ችግር በሚመለከት ረገድ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ:: ለምሣሌ በአገሮች መካከል ስምምነቶችንና መግባባትን በመፍጠር እንዲያም ሲሉ የጦር መሣሪያ ምርቶችን በመቀነስና በመቆጣጠር

በአንድ ዓለማቀፋዊ ቡድን በመታገዝ በሀገሮች ውስጥና መካከል ሊከሰት የሚችለውን የሰላም መደፍረስ ችግር ማስወገድ ይቻላል::

በመጨረሻም በማንኛውም ረገድ በሚወጡ የቀረጥ ደንቦችና ህጎች እንዲሁም ቁጥጥሮች ለማድረግ የተጠናከረና የተባበረ ሕብረ-ብሄራዊ የሆነ እንቅስቃሴ ለመጀመር በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ጥረቶች በሚመጡት ዓሥርተ ዓመታት ወሳኝነት አላቸው:: ከላይ እንደተጠቀሰው ስልጣን ያለው ዓለማቀፋዊ አስተዳደር ለመፍጠር በመጀመሪያ ዓለም አቀፋዊ እውቅና መስጠት በኢኮኖሚና በፖለቲካ የበላይነት በሚንቀሳቀሱ ኃያላን አገሮች ላይ የጋራ መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ብቸኛ አማራጭ ነው::

ተስማሚና አስተማማኝ የሆኑ የአስተዳደር መዋቅሮችንም ለመዘርጋት የተከፋፈለ ስልጣን መስጠት ማለትም በህግ አውጪው በወሳኙና በህግ አስፈፃሚው ምካከል የተወሰነ የራሳቸው የሆነ የሥራ ድርሻ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አግባብ ካላቸው ክፍሎች ጋር ድርድር ለማካሄድ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል:: ለምሣሌ ንግድን በተመለከተ በሚደረገው ድርድር ላይ የአካባቢን ጥበቃ ጉዳይ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው ማስገንዘብ:: በሚፈጠረው አዲስ ዓለማቀፋዊ ግንኙነቶች በመጠቀም ስራዎቹን በመቆጣጠርና አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ ተስማሚና

ገንቢ መንገዶችን ለመቀየስም ይረዳል:: በግለሰብም ሆነ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የኃላፊነት ድርሻና ክልል በተለያየ መጠን መተሳሰርና መጣመር ይኖርባቸዋል:: ነገር ግን እኛ ወደፊት ያለውን ከባድ የቢሮክራሲ ማነቆና የኃላፊነት መደራረብ በተጨማሪም እየተስፋፋ የመጣውን በኃላፊነት ብቁ ሆኖ አለመገኘትን እና የመሳሰሉትን የአሰራር ችግሮች ማስወገድ አለብን::

በግልጽ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚሹ ጉዳዮች ቢኖሩ ከአካባቢ ለሚነሱ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችና አስተዳደሮች ነው:: ምክንያቱም ይህ ሁኔታ በህብረተሰቡና በአካባቢው አስፈላጊ የሆነ ግንኙነትና ቅርርብ ለመፍጠር አይነተኛ መንገድ ነውና:: በሌላ አባባል ይህ ደግሞ የመተጋገዝ ፅንሰ ሃሳብ ነው:: ነገር ግን ትግግዝ ስንል ማንኛውም የአካባቢ ባለስልጣን በራሱ ክልል የሚያስደስተውን ሥራ ለመሥራት ነፃ ነው ማለታችን ሳይሆን ከላይ የሚተላለፉትን ደንብና መመሪያ አስፈጻሚና ተቆጣጣሪ ማለታችን ነው:: ስለዚህ የአካባቢ ስልጣን ተግባር ከዚህ በፊት የተጠቀሱትን መመሪያዎች በመተግበር ላይ ብቻ የተገደበ ነው:: በእርግጥ በተለያየ ደረጃ የተወያየባቸውንና የወጠናቸውን ትልሞች ተግባራዊ ለማድረግ ብሎም ለስኬታማነቱ አስፈላጊውን የሀብት አይነትና መጠን መምረጥና መወሰን ይችላሉ::

በጎረቤት ሀገሮች መካከል በጠቅላላው በምድራችን ላይ ከሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የምናደርገው ግንኙነትና ትስስር እንዲሁም የህዝቡን መብትና ግዴታ ያስከብራሉ ተብለው በሚወከሉ ተመራጮችና በወከላቸው ህዝብ መካከል በአጠቃላይ በምንኖርባት ምድርና በሚመጣው ትውልድ መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነትና ትስስር ከላይ በሰፋት በተጠቀሱት ዋና ዋና መመሪያዎችና ደንቦች ላይ የተመሰረቱ መሆን ይገባቸዋል::

## 4. የድርጊት መመሪያዎቻችን ሊያካትታቸው የሚገቡ ጉዳዮች (ነጥቦች)

ዋና ዓላማው አሁን የሰው ዘር ባጋጠሙት ችግሮች ላይ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነትን ለማረጋገጥ ብሎም ለችግሮቹ መፍትሄ መሻት የማንኛውም ህዝብና ሀገር መሪ ወይም ተቋም ብቻ ሳይሆን የተጨቆኑና ደካማ የሆኑ ህዝቦች በአጠቃላይ የምድራችን ፍጡራን እንዲሁም የመጪው ትውልድ ኃላፊነትና ተግባር መሆኑን ከወዲሁ ማሳወቅ ነው::

በእንገብጋቢ ችግሮች ከመጋፈጥ በተጨማሪ በ19ኛው ምዕተ ዓመት መሲሐዊ እንቅስቃሴዎች በመዳከማቸው ያለንበት ህብረተሰብ ስለወደፊቱ እንዳያስብ ተደርጓል:: ከጊዜ ጊዜ ውስብስብ እየሆነ የመጣው

ህብረተሰባችን አንድ አይነት የለውጥ ሂደት መፍጠርና መተግበር እጅግ ከባድ ሆኖ አግኝቶታል:: እንዲያውም የወደፊቱን ዓለም ሁኔታ ለመምራት ራሱን በበቂ ሁኔታ አላዘጋጀም:: በመሆኑም በተጨባጭ የሚታዩና አንድ ወጥ የሆነ የለውጥ ሂደት መፍጠሩ በጥም አስፈላጊ ነው::

ዛሬ የድርጊት አቅጣጫችንን ከመዘርዘር ባሻገር ለተጨባጭ ተግባራዊ እርምጃ መነሣሣት ተገቢ ነው::

በተጨማሪም ለተግባራዊ ሂደቱ ስኬታማነት ከዜጎችና ከተጠቃሚዎች የፀባይ ለውጥ አንስቶ እስከ አካባቢያዊ የተቀናጀ እርምጃ በአጠቃላይ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው ውሳኔ እስከ ማድረግ ድረስ ባለብዙ ፈርጅ የሆኑ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው:: ይህ ሁሉን አቀፍ የለውጥ ሂደት የሚከተሉትን ነጥቦች ማካተት አለበት::

## ተራማጅ የውክልና ለውጦች

ዓለማችን ከመስከ ትግባሬዎች አስቀድማ በአብዛኛው በአስተሳሰባችን ትለወጣለች:: ትምህርት ለወሳኝ ተግባራዊ እንቅስቃሴም ዓይነተኛ አንቀሳቃሽ ሞተር ሲሆን በእሱም በመታገዝ አያሌ ለውጦችን ማምጣት ይቻላል::

አዲስ እና በውስጡ ጠንካራ ሥነ ምግባር ያለው ሰብአዊነት መፍጠር አለብን:: ከምዕራባዊ ሥልጣኔና የቴክኖሎጂ እንዲሁም የኤኮኖሚ እድገት ይልቅ ለተለያዩ ሥልጣኔዎች ባህላዊና መንፈሣዊ ቅርሶች እንዲሁም ለዕውቀት ቅድሚያ መስጠት አለብን:: በኮሌጆችና በትምህርት ቤቶች የሚሰጠው ትምህርት የትኩረት አቅጣጫው የተለያዩ ቅርሶችን ማጥናትና እነሱንም ወደተጨባጭ እውነታ መቀየር መሆን አለበት:: በተጨማሪም ሳይንስና ቴክኖሎጂን በጥሬነታቸው የመቀበልን ባህል ማስወገድና በዚህም ፋንታ በውድድር ሳይሆን ዘዴ በተመላበት ትብብር ለመቅረብ መሞከር አስፈላጊ ነው::

የዚህም ትምህርት ዓላማ ከዚህ በፊት በነበሩት የትምህርት ይዘቶች ላይ መጨመር ወይም አዲስና በሁሉም ሀገሮች በተመሣሣይ ሊሠራ የሚችል መግቢያ የኤኮሎጂ ኮርስ መቅረጽ አይደለም:: ነገር ግን በሰውና በአካባቢው መካከል ባለው ዝምድናና ልዩነት ላይ ያተኮረ አለማቀፋዊ ይዘት ያለው የትምህርት ሥርዓት መዘርጋት ይሆናል:: የዚህ አይነቱ የትምህርት ሥርዓት ሲዘረጋ ትምህርቱ ለማንኛውም ፍላጎቱ ላለው ዜጋ በተለይም ለአሰልጣኞች ለመምህራን ለጋዜጠኞች ለቴክኒሽያኖችና ለኢንጂነሮች ለውሳኔ ሰጪዎች መሰጠት አለበት::

# የጋራ የወደፊት እይታን መገንባት

ኃይልንና ጥረቶችን ማስተባበርና የአሁን የውሳኔ ብያኔዎች ዘላቂነት እንዲኖራቸው ማድረግ የሚቻለው፡ በጊዜ የተገደበ የጋራ የወደፊት ትልም ሲኖር ብቻ ነው። የጋራ እይታ በወል ፍላጎት ፈቃደኝነት መመርኮዝ ችግሮችን ለመቋቋም እጅግ አስፈላጊ የሆነ ሁለንተናዊነትን ለማፅናት ብሎም ሳንካዎችን ለማለፍና የመፍጠር ክህሎትን ለመተግባር ወሳኝ ይሆናል።

አፋጣኝ የፈጠራ ሥራ፡- ፈጠራ ለብቻው የሚከናወን ድርጊት ሳይሆን አያሌ ውጣ ውረዶችን የሚያካትት ጉዳይ ነው። በአንድ መሥክ ላይ ብቻ ያተኮረ ፈጠራ የመጨረሻው ውጤት ውድቀት ነው። ስለዚህ የቴክኒክ ፈጠራዎች ማህበራዊ ፈጠራዎች እንዲሁም የአስተሳሰብ፡- የባህሪና የተቋም ለውጦች ወደ ተግባር የሚቀየሩት በተያያዘ ሂደት ውስጥ ነው። መንግሥታት ድርጅቶች የገበሬ ማህበራት የሠራተኛ ማህበራት እንዲሁም የተጠቃሚ ማህበራት የቴክኒክና የማህበራዊ ፈጠራዎችን በተመለከተ ለመጪዎቹ አሥርተ ዓመታት የተቀናጀ አመለካከት ማራመድ አለባቸው።

የልምድ ልውውጦችን ማሳደግ:- የማህበራዊና የቴክኒክ ፈጠራዎች በአብዛኛው የሚመነጩት ከአካባቢያችን ነው:: ለምሣሌ:- በማምረቻ ቦታዎች ውስጥ በከተሞች ውስጥ ወይም በመንደሮች ውስጥ ሊሆን ይችላል:: የእነዚህም ፈጠራዎችም መሠረቱ አካባቢያቸው ነው:: ነገር ግን ወደሌላ አካባቢዎችም መሠራጨት መዋሃድና ወደ ተግባር መለወጥ አለባቸው:: ይህ ደግሞ በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል ሰፋ ያሉ ግንኙነቶችን ይፈልጋል:: ይሁን እንጂ እስካሁን በህብረተሰቦች መካከል ያሉ ግንኙነቶች አካባቢያዊና በተወሰኑ ነገሮች ላይ የተወሰኑ ሲሆኑ አብዛኞቹ ችግሮች ግን አለማቀፋዊ ይዘት አላቸው:: ስለዚህ አሁን ያለውን ግንኙነት ማሳደግና አዳዲስ ግንኙነቶች እንዲፈጠሩ ማበረታታት:: ከዚህ በፊት ያየናቸውን ሶስት መሠረታዊ ችግሮች ልናስወገድ የምንችለው በዚህ መልኩ ብቻ ነው:: ወደፊት የምናወጣቸው የሥራ ትልሞች ገጽታ እያደር ቅርጽና መልክ እያያዙ ነው:: ለዚህም የዘዴዎችና የመሣሪያዎች መጣጣም በመፍትሄዎችና በሦስቱ አበይት ችግሮች መካከል ያለው ግንኙነት በተጨማሪም ቅድሚያ የሚሰጣቸው አካባቢያዊና ምድራዊ ችግሮችን በየአህጉሩ ተቀባይነት ካገኙት አስቸካይ ችግሮች ጋር በማጣጣም የተለያዩ ደረጃዎችን ያካተተና የተቀናጀ እርምጃ መውሰድ ወሳኝ ነው::

ይህ ዘዴ በርካታ መስኮችን ይሸፍናል:: ይኸውም የተጠናከረ የአስተሳሰብ የትምህርት:- የተቋሞች:- የቴክኖሎጂ:- የህግ:- የግብር እና የዓለም አቀፍ ግንኙነት ለውጦችን ያካትታል::

## 5. የማስተባበሪያ መርሃ ግብሮች

ወደ 20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እየተቃረበን በመጠን ቁጥር የሰው ልጅ ልዩና አስቸኳይ የሆኑ አለም አቀፋዊ ውጣውረዶች ከፊቱ ይደነቀሩበታል:: እነዚህንም ፈተናዎች ለመወጣት ዋና በሆኑ ችግሮች ላይ ያለውን ኃይል ማስተባበር ይጠበቅበታል:: እነዚህንም ችግሮች ለመቅረፍ የሚወጡት መርሃ-ግብሮች በራሳቸው በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ለውጥ ለማስተባበር ብቃት የሌላቸው ናቸው:: ከዚህም ባሻገር በጋራ ፕሮጀክቶች የሚገለጹ የሥራ እድሎችን መፍጠር ሁሉም ሕዝቦች የአንድ ማህበረሰብ አባል መሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ የጎስቋላ ሕዝባችንን የኑሮ ሁኔታ በሚያስተካክልና በሰው ልጅ እና በአካባቢው ሚዛናዊ እድገትን ማምጣት በሚያስችል ይዘት ሶስቱን መሠረታዊ ችግሮች በአንድ ጊዜ ሊያስወግድ የሚችል በቂ የሆነ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን አያካትቱም::

አምሥት የማስተባበሪያ መርሃ-ግብሮች ያስፈልጉናል:: እነዚህም መርሃ-ግብሮች የሚከተሉትን ጉዳዮች ይመለከታሉ:: ውሃን ኃይልን አፈርን የተራቆቱ አካባቢዎችን መልሶ መገንባትን እና የጦር መሣሪያ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሠላማዊ ምርቶች መቀየር ናቸው::

ውሃ:- በዓላማችን ከሦስት ሰዎች መካከል አንዱ በውሃ እጦት ችግር ይሰቃያል:: ከአሁን በኋላ ሃያ ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ እንደ አፍሪካ በመሰሉ አህጉሮች ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የውሃ ችግር ያጋጥማል ተብሎ ይገመታል::

90 ከመቶ የሚሆኑት ዋና ዋና የሦስተኛው አለም ሀገሮች በሽታዎች የሚመጡት ከንፁህ ውሃ እጦት ነው::

በሀገሮች መካከል የውሃ ምንጮችን ለመቆጣጠር የሚነሱ ግጭቶች ወደፊት እጅግ የከረሩና በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ ክስተቶች ይሆናሉ::

የውሃ አጠቃቀም በአብዛኛው የግጭቶች ምንጭ የመሆኑን ያህል በሕዝቦች መካከል ለሚፈጠር ግንኙነትም መሠረት ነው::

የውሃን አጠቃቀም በሚመለከት የሚወጡ የማስተባበሪያ መርሃ-ግብሮች ከተማዎችን ገጠርን ጤናን እርሻን የኃይል ማመንጫን እንዲሁም የምግብ አቅርቦትን በመንካት የተቀነባበረና መጠነ ሰፊ ይዘት ያለው የሥራ እድልን ይፈጥራል:: ይኸንንም ለማድረግ "ንቁ መደጋገፍ" የሚለውን መመሪያ በመንተራስ ከክልል ደረጃ የሚነሱትን ድምሮች አለማቀፋዊ ይዘት እንዲኖራቸው ማድረግ ያለውን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና ሚዛናዊ የሆነ ግንኙነትን በተፈጥሮና በሰው መካከል ለመፍጠር አይነተኛ እገዛ ያደርጋል::

የኃይል ማመንጫ:- መርሃ-ግብሩ ሁለት ነገሮችን ማካተት አለበት::

- የኃይል ቁጠባና እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የኃይል ምንጮችን ማስተዋወቅ ናቸው:: ሁሉም ሀገሮች ድሆችን ጨምሮ የኃይል ማመንጫዎች አላቸው:: የእነዚህን የኃይል ምንጮች ብቃት ማሳደግ የተቀላጠፈና ኤኮኖሚካል የኃይል ምንጭ ማሳደግ እና ቀስ በቀስ እንደነዳጅ ዘይት ያሉ የቅሬተ-አካላት (fossils) የኃይል ምንጮችን ለመጠቀም የሚደረጉ ድጎማዎችን ማንሳት ዘለቄታነት ያለው የኃይል ምንጭ እንዲኖር ይረዳናል:: ይህ መርሃ-ግብር በከፍተኛ መጠን ሥራ ላይ በሚውልበት ወቅት

እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የኃይል ምንጮችን የማምረት ብቃትን ከፍ ያደርጋል::

ከፍ ብለን የውሃ አጠቃቀም መርሃ-ግብርን በተመለከተ እንዳየነው ሁሉ የሃይል ምንጭም አጠቃቀም "ንቁ መደጋገፍ" የሚለውን መመሪያ በማስተማር ረገድ አስተዋጽኦ አለው::

ይህ-መርሃ-ግብር አካባቢያዊም አለም አቀፋዊም ጠቀሜታ አለው:: ማለትም የአካባቢ ብክለትንና እያደገ የመጣውን የኑኩለየር አደጋን ለመቀነስ ከፍተኛ የሆነ እገዛ ያደርጋል::

አፈር:- ይህ መርሃ-ግብር በአጠቃላይ አፈር ላይ ዝቅተኛ ባየሎጂካዊ የቁጥጥርና የውኃ መዛባት ጉዳቶች ሊያስከትሉ የሚችሉ የእርሻ እና ሌሎች ሥራዎችን ያካትታል::

ዛሬ በአለማችን የተከሰተው የአፈር መራቆት ምርታማነት እያሽቆለቆለ እንዲመጣ የበኩሉን እገዛ ከማድረጉም በላይ የበረሃ መሥፋፋትን አስከትሏል::

የመርሃ-ግብሩ ዋነኛ ጠቀሜታዎች የሚከተሉት ናቸው::

-የሰው ኃይልን በማቀናጀት የድሃ ሀገሮችን የምግብ አቅርቦት ዋስትና ማግኘት:

-ሰፊ የኤኮሲስተም (Ecosystem) ማኔጂመንት ዘዴ መቀየስና

-መለስተኛ ጅምሮችን ከከፍተኛና ሁሉን አቀፍ ከሆኑ መርሃ-ግብሮች ጋር ማቀናጀት ናቸው::

የተራቆቱ አካባቢዎችን እንደገና መገንባት:- ይህ መርሃ-ግብር የሚያካትተው ከዚህ በፊት በኢንዱስትሪ የበለፀጉ አገሮችን ወይም ማዕከላዊ አውሮፓንና፣ የቀድሞዋ የሶቪየት ግዛቶች እንዲሁም የሥልጣኔና የኢንዱስትሪ መስፋፋት ሰለባ የሆኑ ሀገሮችንም ይጨምራል::

ይህ መርሃ-ግብር ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚኖረው የራሳቸውን አካባቢ በትክክል ካለመረዳት ወደተለያዩ አቅጣጫዎች የመሄድ ዝንባሌ ላላቸው ሕዝቦች ነው:: የመልሶ ማቋቋም ትልሞች አዳዲስ ሥፍራዎችን በወረራ ከመያዝ ህልም ባሻገር መታየት አለበት:: መልሶ ማቋቋም አዲስ የሰብአዊነት ድንበር ነው::

# የጦር መሣሪያ ምርቶችን ወደ ሠላማዊ ምርቶች መቀየር

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ የአብዛኛው ሀገሮች የኢኮኖሚ ማዕከል ያደረገው የጦር መሣሪያ ምርትን ነው:: የቀዝቃዛው ጦርነት ፍጻሜ በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ የተፈጥሮንና የሰው ኃይልን ነፃ መውጣት አብስሮዋል:: ነገር ግን ከጦርነት ወደ ሠላም የሚደረግ ሽግግር በርካታ ችግሮች ያጋጥሙታል:: የፖለቲካ መግባባት የቴክኒክ ዕውቀትን የአዳዲስ ገበያዎች መከፈትን እንዲሁም ለቴክኒክ ዕውቀትና ችሎታ ነፃ እንቅስቃሴ እንዲኖር ያደርጋል::

እኛ የጦር-መሣሪያ የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ለእድገትና አካባቢን ወደ ሚጠቅም ኢንዱስትሪዎች እንዲለወጡ የሚያደርግ አለም አቀፋዊ መርሃ-ግብር እንዲኖር ሃሳብ እናቀርባለን:: ይህ ደግሞ ከፍተኛ መጠን ያለው የመጀመሪያ መዋለ ነዋይ ማፍሰስ ያስፈልጋል::

ከዚህ በተጨማሪ ይህ መርሃ-ግብር ከፍጥጫና ከወረራ ዘመን ይልቅ በሕዝቦች መካከል እንዲሁም በሕዝቦችና በተፈጥሮ መካከል ወደ ሚደረገው

የመተጋገዝና የመደጋገፍ ዘመን መሸጋገርን ያበስራል:: ነገር ግን የፀጥታው ሁኔታ በአለም አቀፍ አካላት ዋስትና ሊያገኝ ይገባል:: በተለይም አካባቢያዊና በሀገሮች መካከል እንዲሁም አናሳ ብሄሮችን በተመለከተ::

በእርግጥ የማስተባበር መርሃ-ግብሮች አዲስ አይደሉም:: ከዚህ በፊት የተጀመሩ ተመሣሣይ መርሃ-ግብሮች ውጤታማ አለመሆን ለጥራጣሬ በር ሊከፍት ይችላል:: ነገር ግን እኛ ከአለፈው ስህተቶች በመማር አዲሱን መርሃ-ግብር ለመተግበር አዳዲስ መመሪያዎችን ማውጣት ይኖርብናል::

<u>ለምሣሌ:-</u>

- መርሃ-ግብሩና የሚተገበርበት አካባቢ ችግሮች መጣጣም ይኖርባቸዋል (ልክ ሁለተኛው የዓለም ጦርነትና አውሮፓ ሀገሮች ላይ ያደረሰውን ችግር ለማስወገድ የወጣውን የማርሻል ፕላን የመሰለ)
- አስፈላጊ ከሆነ ሁሉንም ትውልድ ሊያካትቱ የሚችሉ የረጅም ጊዜ እቅዶችን ከ15 እስከ 20 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ መዘርጋት::
- በየደረጃው የገንዘብ አፈሳሰስን ስርዓት መቀየስ:

- የተቋማትን ያልተነካ ኃይልና ከህዝቡ የሚፈልቁ ቴክኒኮችንና ግንዛቤዎችን ማቀናጀትና በተጠሪዎቻቸው አማካኝነትም መግባባት የተደረሰባቸውን ውሎች ማስተባበር::
- በጣም ተስማሚ የሆኑ ቴክኒካዊ መፍትሄዎችን መሠረት በማድረግ ቀስ በቀስ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ማስተዋወቅና ያላቸውንም ተፅዕኖ ከሚመለከተው ህዝብ ጋር በቅርብ በመገናኘት መደበኛ ግምገማ ማድረግ::

ስለዚህ ስኬታማነት ሀብታም ሀገሮች ከፍተኛ እገዛ ማድረግ አለባቸው:: ይህም እገዛ የአካባቢውን የአየር ሁኔታ እግምት ውስጥ በማስገባት ቀረጥ ሊሰበሰብ ይችላል:: እንዲሁም የኃይል አጠቃቀምንና ለጦር-መሣሪያ የሚወጣውን ወጪ ግምት ውስጥ በማስገባት ከእስቶክ ገበያ ገቢዎች ማግኘት ይቻላል::

## 6. ዓበይት ዕቅዶች:-

ሦስት ዓበይት ነጥቦችን መለየት እንችላለን:-

- በሁለት ሺህ ዓ.ም. "በምድራችን ጠቅላይ መንግሥታት" ስር በመሆን ለምናደርገው የተጠናከረና የተቀናጀ የኃይል የማስተባበር ችሎታችን ምስጋና ይግባውና በጣም አንገብጋቢና ዋና በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የምናስተላልፍበትና መርሃ-ግብሮቻችን በስራ ላይ የሚተረጎሙበት ወቅት ይሆናል::

- ከ2030 - 2050 ዓ.ም. ያለው ጊዜ:- ወሳኝ አዲስ ምዕራፍ የሚጀመርበት ነው:: ምክንያቱም የአሁኑ አዝማሚያዎች ወደ ከፋ ሁኔታ ስለሚያመሩና ያለውንም አለመመጣጠን ሊስተካከል በማይችል ሁኔታ ስለሚያባብሱት ቢአብዛኞዎቹ መስኮች በተለይም በስነ-ሕዝብ በማህበራዊ ትስስር በውሃና በኃይል ምንጭ አጠቃቀም ጉዳዮች ላይ አስተማማኝ እና ቀጣይነት ያላቸው የድርጊት አቅጣጫዎች መነደፍ ይኖርባቸዋል::

- **ከ2080 - 2100 ዓ.ም. ያለው ጊዜ:-** በዚህ ጊዜ በሰውና በፕላኔታችን መካከል አዲስ መመጣጠን እንጠብቃለን በተለይ የቀረጥ ብያኔዎችን እና የፋብሪካ ዝቃጭን ማስወገድና ወደተስተካከለ መጠን የሚያደርሱ የኑሮ ዘይቤዎችና የአመራረት ሥልቶችን መቀየስ ይጠበቅብናል::

ዲሴምበር **1993**

*Addis Ababa University Printing press*